የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Office of the Federal Auditor General

ቁጥር Ref. No OFAG.F.06.27/36

ቀን Date 08/02/2017

ለተከበሩ ዶ/ር ፍጹም አሰፋ
የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ

ለክቡር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ
የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር
<u>አዲስ አበባ</u>

ለክብርት ዶ/ር ኡባህ አደም
የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት
<u>ድሬዳዋ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲን የ2015 በጀት ዓመት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማስፈጸሚያ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ይመለከታል፤</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን ዩኒቨርሲቲ የ2015 በጀት ዓመት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማስፈጸሚያ ሂሳብ የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 2 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 2 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 4 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከማክበር ሰላምታ ጋር!

ሰለሞን መብራቱ
የከፍተኛ ትምህርት ተ...
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬ...

የመ.ሣ.ቁ./P.O.Box 457
ስልክ/Tel. +251115573701 +251115574057
+251115573550 +251115574300
ኢ.ሜይል/E-mail ofagit@ethionet.et

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# በትምህርት ሚኒስቴር የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

## የ2015 በጀት ዓመት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና

## ማስፈጸሚያ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

መስከረም 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

**በትምህርት ሚኒስቴር የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ**

**የ2015 በጀት ዓመት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና**

**ማስፈጸሚያ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት**

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ለ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማስፈጸሚያ የተመደበለትን ሂሳብ በፋይናንስ አዋጁ፣ ደንቡ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሰረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማስፈጸሚያ ሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 እና በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1146/2011 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዓለም አቀፍ ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው።

እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል።

የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማስፈጸሚያ ሂሳብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ፣ አጥጋቢ ማረጋገጫና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ በሪፖርቱ ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ይሁን የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው።

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን ወስዶ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት በዩኒቨርሲቲው የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች፡-

- የሂሳብ ማመዛዘኛ ማጠቃለያ፣
- የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማስፈጸሚያ ወጪ ሂሳብ ማጠቃለያ ሪፖርት፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የዩኒቨርሲቲው የ2015 በጀት ዓመት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ማስፈጸሚያ ሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በዩኒቨርሲቲው የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል።

08/02/17

ሰለሞን መብራቱ አትሬሶ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

መስከረም 2017 ዓ.ም

ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
ፕሬዝዳንት

Dire Dawa —University
President

☎ 0251 - 11- 86- 82 ✉ 1362 ፋክስ 025-1-12-79-71 ድሬዳዋ ኢትዮጵያ
E-Mail:ddu1@ethionet.et FAX Dire Dawa Ethiopia

Ref ቁጥር ድ/ዳ/ዩ/101/323/2016
Date ቀን መጋቢት 2/2016 ዓ.ም

ለ፡- ፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ሂሳብ እንቅስቃሴ ሰነድ ስለመላክ፣

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የ2015 በጀት ዓመት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና የሂሳብ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ሰነዶች ከዚህ ደብዳቤ ጋር 2 ገጽ ሪፖርት አያይዘን የላክን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

1. የሂሳብ ማመዛዘኛ ማጠቃለያ ሪፖርት 1 ገጽ
2. የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ማጠቃለያ ሪፖርት 1 ገጽ

ከሠላምታ ጋር

ዶ/ር ኡባህ አደም
ፕሬዝዳንት

Federal Democratic Republic of Ethiopia Dire Dawa University

Federal Government Of Ethiopia

# Monthly Trial Balance Summary by Reporting Unit

15/00/000/323/03/01 - Educational Assesment and Examination Service - Preparing and Delivering Exams

Bank Account: 0001

Accounting Period Status : Closed

Month/Year :Sene / 2015

Print Date : 08/03/2024

(Figures in Birr)

| Account Code | Description | Last Period YTD Debit | Last Period YTD Credit | This Period Debit | This Period Credit | YTD Debit | YTD Credit |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1000-3999 | Revenue/Assistance/Loan | - | 200,168.47 | - | - | - | 200,168.47 |
| 1000-1999 | Items of Domestic Revenue | - | 200,168.47 | - | - | - | 200,168.47 |
| 1000-1399 | | - | 200,168.47 | - | - | - | 200,168.47 |
| 1100-1119 | | - | 200,168.47 | - | - | - | 200,168.47 |
| 1101 | Wages and Salaries | - | 200,168.47 | - | - | - | 200,168.47 |
| 6000-6999 | Items of Expenditure | 27,830,310.51 | - | 381,123.75 | 613,778.88 | 27,597,655.38 | - |
| 6100-6199 | Personnel Services | 1,337,283.51 | - | 368,733.75 | - | 1,706,017.26 | - |
| 6110-6119 | Emoluments | 1,337,283.51 | - | 368,733.75 | - | 1,706,017.26 | - |
| 6116 | Miscellaneous Payments to Staff | 1,337,283.51 | - | 368,733.75 | - | 1,706,017.26 | - |
| 6200-6299 | Goods and Services | 26,493,027.00 | - | 12,390.00 | 613,778.88 | 25,891,638.12 | - |
| 6210-6229 | Goods and Supplies | 6,481,640.13 | - | - | 492,818.75 | 5,988,821.38 | - |
| 6214 | Medical Supplies | 304,177.78 | - | - | 304,177.78 | - | - |
| 6216 | Food | 6,053,377.35 | - | - | 64,555.97 | 5,988,821.38 | - |
| 6219 | Miscellaneous Equipment | 124,085.00 | - | - | 124,085.00 | - | - |
| 6230-6239 | Travelling and Official Entertainment Services | 14,909,330.33 | - | 12,390.00 | 120,960.13 | 14,800,760.20 | - |
| 6231 | Per Diem | 10,011,214.54 | - | 12,390.00 | - | 10,023,604.54 | - |
| 6232 | Transport Fees | 4,789,545.66 | - | - | 12,390.00 | 4,777,155.66 | - |
| 6233 | Official Entertainment | 108,570.13 | - | - | 108,570.13 | - | - |
| 6250-6259 | Contracted Services | 5,102,056.54 | - | - | - | 5,102,056.54 | - |
| 6251 | Contracted Professional Services | 5,081,880.00 | - | - | - | 5,081,880.00 | - |
| 6255 | Freight | 7,776.54 | - | - | - | 7,776.54 | - |
| 6258 | Telecommunication Charges | 12,400.00 | - | - | - | 12,400.00 | - |
| 4000-4099 | Transfer | - | 27,759,478.92 | 361,992.01 | - | 361,992.01 | 27,759,478.92 |
| 4000-4049 | Cash Transfers | - | 27,759,478.92 | 361,992.01 | - | 361,992.01 | 27,759,478.92 |
| 4002 | Recurrent Operating Expenditure | - | 27,759,478.92 | - | - | - | 27,759,478.92 |
| 4009 | Other Cash Transfers | - | - | 361,992.01 | - | 361,992.01 | - |
| 4100-4199 | Cash and Cash Equivalents | 129,336.88 | - | - | 129,336.88 | - | - |
| 4103 | Cash at Bank | 129,336.88 | - | - | 129,336.88 | - | - |
| 4100-4999 | Assets | 129,336.88 | - | - | 129,336.88 | - | - |
| | Total | 27,959,647.39 | 27,959,647.39 | 743,115.76 | 743,115.76 | 27,959,647.39 | 27,959,647.39 |

# Recurrent Expenditure By Budgetary Institution And Item of Expenditure

## Federal Government Of Ethiopia

## 15/00/000/323/03/01 - Educational Assesment and Examination Service - Preparing and Delivering Exams

Account Code : 6000-6999 | Month/Year : Sene / 2015

Source of Finance : Treasury(1800) | Accounting Period Status : All

Print Date : 08/03/2024

(Figures in Birr)

| PB | Prg. | SA | SP | Proj. | Description | Approved Budget | Supplements | Transfer Added | Transfer Deducted | Net Adjustment | Adjusted Budget | Actual Expenditure | Over / Under |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | Total | - | - | - | - | - | - | 27,597,655.38 | (27,597,655.38) |
| 323 | | | | | Educational Assesment and Examination Service | | | | | | | | |
| | 03 | | | | Examination Preparetion,Result Correction, Compilation and Student Placement | | | | | | | | |
| | | 01 | | | Preparing and Delivering Exams | - | - | - | - | - | - | 27,597,655.38 | (27,597,655.38) |
| | | | | | 6116 - Miscellaneous Payments to Staff | - | - | - | - | - | - | 1,706,017.26 | (1,706,017.26) |
| | | | | | 6214 - Medical Supplies | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | | | | | 6216 - Food | - | - | - | - | - | - | 5,988,821.38 | (5,988,821.38) |
| | | | | | 6219 - Miscellaneous Equipment | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | | | | | 6231 - Per Diem | - | - | - | - | - | - | 10,023,604.54 | (10,023,604.54) |
| | | | | | 6232 - Transport Fees | - | - | - | - | - | - | 4,777,155.66 | (4,777,155.66) |
| | | | | | 6233 - Official Entertainment | - | - | - | - | - | - | - | - |
| | | | | | 6251 - Contracted Professional Services | - | - | - | - | - | - | 5,081,880.00 | (5,081,880.00) |
| | | | | | 6255 - Freight | - | - | - | - | - | - | 7,776.54 | (7,776.54) |
| | | | | | 6258 - Telecommunication Charges | - | - | - | - | - | - | 12,400.00 | (12,400.00) |
| | | | | | 6417 - Grants and Gratuities to Individuals | - | - | - | - | - | - | - | - |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Dire Dawa University